# መደራጀት ወሳኝ ነው — ድርጅት ግን ምንድነው?

ከመላኩ ይስማው

ከዚህ ሁሉ ተመክሮ በኋላ መደራጀት አያስፈልግም የሚሉና የሚከራከሩም መኖራችው ያስገርማል -- ግን አሉ! በዚህም በዚያም፣ የአምላክም ድጋፍ ተጨምሮብት፣ አንድ ጀግና አውጥተን በእሱ መሪነት (በእሷ አይባልም ብዙ ጊዜ) እንታገል ይላሉ። ይህ ደግሞ ከዚህ በታች ለማሳየት እንደምሞክረው የድርጅትን ምንነትና ለትግልም ምን ይጎዳል ምን ይጠቅማልን አለማወቅ ነው ባይ ነኝ።

ድርጅት ሰው ሰው ከሆነበት ጊዜ ጀምሮ የታየና የመጣ ነው። ተጋቡ ራሱ ተደራጁ ነው። ሁለት ሰዎች ትዳር በሚሉት ጥላ ሥር፣ በተስማሙባቸው የወል መርሆች ሕይወትን እየተረዳዱ የሚመሩበት። ቤተሰብም ድርጅት ነው — ስነስርዓት ነው፤ ስነምግባር፤ የጋራ ግዳጅና ሀላፊነትም አለው። እነኝህም ናቸው በሌላው የአካባቢያቸው ኗሪ ውስጥ የዚያን ቤተሰብ አባላት በራሳቸው ንዑስ ስብስብ ውስጥ አያያዘው የሚያቆዩዋቸው። አርሶ አደር በደቦ ይደራጃል፣ ዕድርና ዕቁብም ድርጅቶች ናቸው። ድርጅት ሰዎች ከመሰላቸው ጋር ሆነው መሰረታዊ ችግሮችና ጋሬጣዎችን የሚጋፈጡብት ነው ማለትም ይቻላል። የጋራ ጥረት ነጸብራቅ ነው። ድርጅት በቅድሚያ የትብብርና የመሰባሰብ ፍላጎት ውጤት ነው። በወል ዓላማ ሥር ተሰባስበው በተስማሙበት የተፃፈም ሆነ ያልተፃፈ የወል ደንባቸው እየተገዙ በጋራ ሊሰሩ፣ ሊንቀሳቀሱ። ተሰባስበውም የጋራ ዓላማ ለማሳካት።

ወደ ፖለቲካው ስንመጣ ደግሞ የተለየ የራሱን ይዘትና ጠባይ ይይዛል። የፖለቲካ ድርጅት ዕቁብ ወይም ዕድር አይደለም። ማህበራዊ ድርጅትም (የሰራተኛ፤ የተማሪ፤ የአስተማሪ፣ የሴቶች፣ የወጣቶች ወዘተ) አይደለም። ይህን ያልተረዱ ከሕዝባዊ ድርጅቶች የፖለቲካ ድርጅት ሚናን ይጠብቃሉ። ወይም በተገላቢጦሽ። የፖለቲካ ድርጅት መረዳጃ ማህበር ወይም ተባብሮ እርሻ ደቦ ማለትም አይደለም። የፖለቲካ ድርጅት በምን ይታውቃል?

- የሚደራጀው የፖለቲካ ዓላማን ከግብ ለማድረስ ነው፣

- የራሱ የሆነ አወቃቀር አለው፣
- መሰባሰቢያው ፖለቲካዊ መርሀ-ግብር ነው፣
- የመጨረሻ ግቡም ፖለቲካዊ ለውጥንና ስልጣንንም የሚመለከት ነው።

ድርጅቶች ለፖለቲካ ስልጣን ነው የሚታገሉት በሚል ክስ ሊደረድሩ የሚሞክሩ አሉ። ትግሉ የማንን ጎፈሬ ለማበጥር ነው ታዲያ የሚለው የዕቅጩ መልስ እዚህ ላይ ቦታው ነው። ማንም የፖለቲካ ፓርቲ የፖለቲካ ሥልጣን ለመያዝና የፖለቲካ መርሀ-ግብራቸውን ተግባር ላይ ለማዋል እራሳቸውን በአንድነት ያደራጁ ሰዎች ስብስብ ነው። ቆመንለታል የሚሉት ሀገር ምን ዓይነት መንግሥታዊ አስተዳደር ሊኖረው እንደሚገባ የሚስማሙባቸው እሳቤዎች በመካከላቸው ይኖራቸዋል። ለዚህ መሣካት በወል ይሰራሉ። በወል ለመሥራትና እንቅስቃሴያቸውን ለማቀናጀት ደግሞ የግድ ይላቸዋልና ሁሉም የሚገዙበትና ሁሉም የሚያያዙበት ደንብና ድርጅታዊ መዋቅር አላቸው።

እርግጥ ነው ድርጅት ከድርጅት ይለያል -- የየሀገሩ ተጨባጭ ሁኔታ አንድ አይደለምና። ይህ ሀቅ ቢሆንም የፖለቲካ ድርጅቶች የሚጋሩት ይዘት አላቸው። ቀደም ሲል እንደተገለጸው ግብና ዓላማን ማወቅ፣ ስነስርዓት ማክበር፣ አመራርና አባላትን የሚያስተባብር ህገ ደንብ መያዝ፣ የሚሰራ መዋቅርን መገልገል ወዘተ ድርጅትን ይገልጹታል። ሁሉም የፖለቲካ ፓርቲዎች/ድርጅቶች ርዕዮተ-ዓላማቸው **(ideology)** የሚገለጽበት፣ ሥልጣን ሲይዙም ተግባራዊ የሚያደርጓቸው ፖሊሲዎች የሚቀመጡበት የፖለቲካ መርሀ-ግብር ይኖራቸዋል።

ከዚህ እውነታ በተቃራኒ "ከቆራጡ እና ብቸኛው አንዱ መሪያችን ጋር" መፈክር ለሕዝባዊ ትግል ዛሬም እንደትላንቱ ሊያሸክሙት የሚሰብኩ አይጠፉም። ከመርህ አንፃር ለዴሞክራሲ የሚታገሉ ድርጅቶች የኋላቀርነትን መርህ ይዘው በአንድ ቆራጥ መሪ ስር የሚጓዙ ሊሆኑ አይችሉም። ገና ከመጀመሪያው አንድ ቆራጥና ሁሉን አዋቂ መሪ የሚለው ጽንሰ ሀሳብ የሕዝብን ሚና የሚቀማና አምባገነናዊ አቅዋሞችን ጋባዥ ነው። እሳቸው በሚባል ግለሰብ ስር ህልውናቸው ሲገለጽ የቆዩ ድርጅቶች ከስመዋል ወይም ሚናቸው ደቃቅ ሆኖ ቀርቷል። ካባ የተጠለቀላቸው

ግለሰቦችም ሳይውል ሳያድር ብቃቱም፤ ጽናቱም ሆነ ቆራጥነቱም የሌላቸው ሆነው ተገኝተው ሕዝብን አሳፍረዋል። ጫጫታው እንዳይበዛ እገሌ እገሌ ከማለቱ እቆጠባለሁ። አላፊው አግዳሚው አባል የሚሆንበት ድርጅት አይደለም። በሚገባ ተዋቅሮ ማነው አባል ማነው ያልሆነ የሚለውን መመለስ ያቃተውም ድርጅት ሊባል ኣይገባውም። ወደ ኋላ መለስ ብለን ካየን ድርጅት ነን ብለው ግን የድርጅትን ይዘት ማንጸባረቅ ያልቻሉ ሁሉ ሲጠቁና ትግልንም ሲጎዱ ታዝበናል። ድርጅት ከአንድ ቀን፣ ከሞቅ ሞቅ ሰልፍ በላይ ነው። መዋቅር የግድ ነው። ህግና ድንብ ያስተሳስራቸው አባላት መኖር አለባቸው። በድርጅቱ ስራ የሚሳተፉ አባላት መኖር አለባችው — መዋጮ መክፈል ብቻ ሳይሆን በድርጅቱ መመሪያ መሰረት የሚንቀሳቀሱ። ሳር ቅጠሉ አባላችን ነው ጨዋታ የድርጅትን መኖር መጠናክር አያሳይም።

እርጥብ ከደረቅ፣ ወደግራ ከወደ ቀኝ፣ ወደፊት ከወደ ሁዋላ፣ እንፉታ ከእንጋባ፣ እገሌ ከእገሌ ሳንል፣ ሆ ብለን እንታገል የሚልም ሃሳብ ሲቀነቀን ይስተዋላል። ብቃት ያለው ፖለቲካ ስብስብ ለመሆን የሚያስፈልጉ ነገሮችን ሳያሟላ እንደምን የተዋጣለት የፖለቲካ ሥራ ሊያካሂድ እንደሚችል ግራ ይገባል። የጠላትን አቅምና ስልት ከግምት ያስገባ አይደለም። እስከአሁንም በሀገራችን የተቃዋሚው ጎራ የሄደበትን መንገድ ልብ አለማለት ነው። የአገዛዙ እና የውጭ ጌቶቹ፣ ከራሳቸው ብሔራዊ ጥቅም አንፃር በሀገራችን ላይ ተጽዕኖ ማሳደር የሚሹ ሌሎች ሃይሎች መኖራቸውንም መርሳት። እነኝህም ሃይሎች በግልጽም፣ በስውርም፣ በመመሳሰልም በትግሉ ላይ ጉዳት ለማድረስ ወደሁዋላ እንደማይሉ መገንዘብ አለብን። ያለፉትን አመታትም ትግሉ በወያኔ ሜዳ ክልል ሳይሆን በተቃዋሚው ሜዳ ክልል እንዲሆንና ተቃዋሚው ጎራ እርስ በርስ እየተጣላ እንዲያሳልፈው እንዴት እንዳደረጉ እስኪ ቆም ብለን እናስበው። በአጠቃላይ ቀደም ሲል የተመለከቱትን አላባዊያን - ግብና ዓላማን ማወቅ፤ ስነስርዓት ማክበር፤ አመራርና አባላትን የሚያስተባብር ህገ ደንብ መያዝ፤ የሚሰራ መዋቅርን መገልገል — ባላሟላ አመራር ትግል አካሂዳለሁ ማለት ተከታይን ለሀገር ውስጥም ሆነ ለውጭ ጠላት ለከፋ አደጋ ማጋለጥ፣ የአባላትን መሥዋዕትነት ማብዛት፣ ሊበራ ይችል የነበረው ሕዝባዊ አመጽ ላይ ባላዋቂ ሳሚነት ውሀ ማፍሰስ ይመስለኛል።